# አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ

## ሕግና አስተዳደር ትምህርቶች ኮሌጅ

# *የዓድዋ ድል ለዛሬው የኢትዮጵያ፣ የአፍሪካና የዓለም ሕዝቦች*

# *የሚጠቁመው የመልስ አቅጣጫ*

ለወ/ሪት ዝምታ ጐርፉ ማስታወሻ በገ/ኢ ጐርፉ
የሥነጽሑፍ ውድድር ኣሸናፊ ድርሰት

ስም ……………………..ገብረሕይወት ቸኮለ

የመታወቂያ ቁጥር…………. LGR/8613/08

ስልክ………………………0909603973

## መግቢያ

በዚህች አጭር ፅሑፍ የዓድዋ ድል ለዛሬ የኢትዮጵያ፣ አፍሪካና የዓለም ጥያቄዎች ምን የሚመልስ አቅጣጫ እንደሚያስቀምጥ ተብራርቷል። ፅሑፉ የዓድዋ ድል ምን እንደሚመልስና ለዓለም፣ አፍሪካና ኢትዮጵያ ሕዝቦች ነፃነት ያበረከተውን ሚና ከታሪክ ማኅደር በማስቃኘት ይጀምራል። ቀጥሎም ወደ ዋናው ርዕሰ ጉዳይ በመግባት ድሉ ለኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካና ለዓለም ጥያቄዎች የሚያስቀምጠውን የመልስ አቅጣጫ ይተነትናል።

## አጠቃላይ

የዓድዋ ድል ለዛሬው ኢትዮጵያ፣ አፍሪካና ዓለም ሕዝቦች የሚጠቁመውን የመልስ አቅጣጫ ከማስቀመጣችን በፊት ስለ ዓድዋ ድል ከታሪክ ማኅደር በወፍ በረር መዳሰሱ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ለኢትዮጵያ፣ አፍሪካና ዓለም ለምናስቀምጣቸው የዘመኑ የመልስ አቅጣጫዎች መሰረቱ ነውና።

የዓድዋ ድል በኢትዮጵያ አቆጣጠር በየካቲት 23 1888 ዓ.ም. እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር ደግሞ በ1896 ዓ.ም. በኢትዮጵያና ጣሊያን መካከል በተደረገው ጦነርት በኢትዮጵያ አሸናፊነት የተገኘ ድል ነው። ጦርነቱ በብዙ ምክንያቶች የተነሳ ቢሆንም በኢትዮጵያና ጣሊያን የተፈረመው የውጫሌ ውል የቅርብ መንስኤው ነበር። የውጫሌ ውል ዓንቀጽ ዓስራ ሰባት የጣሊያንኛው፡- ኢትዮጵያ ከአውሮጳ መንግሥታት ጋር የምትፈልገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግስት በኩል ብቻ ማድረግ አለባት ሲል፤ አማርኛው ደግሞ ኢትዮጵያ ከአውሮጳ መንግሥታት ጋር የምትፈልገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግሥት በኩል ማድረግ ትችላለች ይላል። የአማርኛው የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና ልዕልና ያከብራል፤ የጣሊያንኛው የኢትዮጵያን ሉአላዊነትና ልዕልና መድፈር ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ክብሯንና ጥቅሟን ይነካል። ይኽን የተገነዘቡት የኢትዮጵያ መሪዎች የውሉ ዓንቀጽ ዓስራ ሰባት የጣሊያንኛ ትርጓሜ የኢትዮጵያን ክብርና ጥቅም በማይነካና ሉአላዊነቷን በሚያከብር መልኩ እንዲስተካከል በተደጋጋሚ ወተወቱ፡ መወትወቱ ውጤት ሳያመጣ ቢቀር፤ "ምኒሊክ፡ መዘግየት አደገኛ ነው።" አሉ ጣይቱ። ስለዚህ ጉዞ ወደ ወሳኙ ጦርነት ማድረግ የግድ ነበር። ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያለምንም የዘር፣ የቋንቋና የሃይማኖት ልዩነት ወደ ዘመቻው በማስገባትም ለወረራ የመጣውን የጣልያን ወታደር ድል በማድረግ አሳፍረው መለሱት። በዘመቻውም ኢትዮጵያውያን ለአንድነታቸው በጋራ ያለ ምንም ልዩነት ስለተነሱ ጦርነቱን በድል አጠናቀቁ። በኢትዮጵያ አሸናፊነት የጣልያን የቅኝ ግዛት ማስፋፋት ሕልም ተኮላሸ።

ከጦርነቱ በፊት እ.ኤ.አ. በ1880ዎቹ መጀመሪያ በጀርመን አገር በርሊን ከተማ ላይ በተደረገው የአውሮጳ ቅኝ ገዢ (ኮሎኒያሊስት) መንግስታት ባለሥልጣናትና ልሂቃን የጦር ጄኔራሎችና ሊቃውንት ስብሰባ ላይ "ጥቁር ሰው ትልቅ ትል ነው፣ ቅንቡርስ ነው እንጂ ነፍስ ያለው ሰው አይደለም" ሲሉ የነበሩት አፈሩ፤ እውነትና ፍትሕ ኢትዮጵያና አፍሪቃ ከበሩ። ከሲግመንድ ፍሮይድ የሳይኮ-አናሊሲስ ጥናትና ምርምር በፊት፡- ጥቁር ሕዝብ ትልቅ ትል

ላይሆን ነፍስ ያለው ሰው ከሰውም ሰው ጀግና መሆኑን በተጨባጭ ያስመሰከረ የኢትዮጵያ ገበሬ ሠራዊት ነበር።

ከአውሮጳ መንግሥታት ሩሲያና ፈረንሳይ የዓድዋን ድል ከልብ ደገፉ። ጀኔራል ባራቴሪ በአገሩ በኢጣሊያ ጦር ፍርድ ቤት ቀርቦ ማዕረጉ ተገፈፈ። የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲኞር ክሪስፒ በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ለቀቁ። የእንግሊዝ ጋዜጦች በዓድዋ ድል ማግስት የዓለም ታሪክ ተገለበጠ፣ ታላቅ የትውልድ ኃይል በአፍሪቃ ተቀሰቀሰ ብለው ጻፉ። በኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ፡- ዘመናዊት ኢትዮጵያን የፈጠረ የተባሉት ዳግማዊ ዓፄ ምኒሊክ በሌሉበት (በአካል ባልተገኙበት የነፃነት ተጋድሎ መሪዎች ጉባኤ) የአፍሪቃና የመላው ዓለም ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተጋድሎ መሪ ተብለው ተሰየሙ።

የዓድዋን ድል ለማምጣት አትዮጵያውያን ያለምንም የዘር፣ የብሔር፣ የሃይማኖት፣ የፆታና ሌሎችም ልዩነቶች ሳይበግሯቸው በጋራ ዘምተዋል። በዘር፣ በቋንቋና ሃይማኖት ልዩነቶች ሊከፋፍላቸውና ሊቀራመታቸው የመጣውን የጠላት ኃይል ድል በማድረግ አሳፍረው መልሰዋል። በዓድዋ ዘመቻ ኢትዮጵያውያን ለብሔራዊ አንድነታቸው ሕይወታቸውን ሰውተዋል። ሕገ-ወጡንና የሰብአዊና ዲምክራሲያዊ መብቶችን የገረሰሰውን ቅኝ ግዛት በመቃወም ኢትዮጵያውያን ለዓለም ሕዝብ በሙሉ ፈለግና አርአያ ሆነዋል። የሰው ልጆችን ሰብዓዊነትና ነፃነት የሚጋፋውን ቅኝ ግዛት በማምበርከክ በዓለም ላይ ለተጨቆኑ ሕዝቦች ሁሉ የመወጣጫ ድልድይና መሰላል በማዘጋጀት ለሰብአዊነታቸውና ነፃነታቸው በር ከፍተዋል።

ድሉ የጣሊያን መንግስት ቅኝ ግዛትን ሕጋዊ ለማድረግ ከአውሮጳ ጀምሮ መጥቶ የሰው ልጆችን ሰባዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለመጣስ መጥቶ አንገት ደፍቶ የተመለሰበት ወርቃማ ድል ነው። ድሉ የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የመላው አፍሪካውያን ብሎም በዓለም ለተጨቆኑ ሕዝቦች ነበር። ከዓድዋ ድል በኋላ በዓለም ላይ የሚኖር የተጨቆነና ቅኝ የሚገዛ ሕዝብ በሙሉ ለነፃነቱ መታገል እንደሚችልና ሕገወጥነትን ድል ማድረግ እንደሚቻል ተረድቷል። ለመብቱና ነፃነቱም ተነሳስቷል። ድሉ አፍሪካን ወደ አንድ በማምጣትና ለትግሉ ዝግጁ እንዲሆኑ በማድረግ ከፍተኛ የሆነ የሞራል ስንቅ ሆኗል። የተለያዩ ተቋሞችና ንቅናቄዎች እንዲነሱ በማድረግ አፍሪካውያንና መላው በዓለም የሚኖር ጥቁር ሕዝብ ሁሉ ለነፃነቱ እንዲታገል አድርጓል። የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያን የነፃነት

ፋና-ወጊና የጀግንነታቸው፣ የአንድነታቸውና የጥንካሪያቸው ምንጭና ምስክር ነው። ለመላው አፍሪካውያናን ጥቁር ሕዝቦችም የሞራላቸው ስንቅና የነፃነታችው ምልክት ነው። ከዓድዋ ድል በሆላ በአፍሪካ፣ በእስያና ሌሎችም አህጉራት የሚኖሩ የጥቁር ሕዝቦች ነፃነታቸውን አውጀዋል። አፍሪካ የራሷን ታሪክ መመዝገብ ካለባትና ለትውልድም ያልተበረዘውን ማንነቷንና ነፃነቷን ማስተላለፍ ከፈለገች የዓድዋን ድል መዘከርና ማስታውነስ ይኖርባታል። የዓድዋ ድል የጥቁር ሕዝቦች መርህና የወደፊትም ዕቅዳቸው ሊሆን ይገባል።

በአፍሪካ ለተመሰረቱት ንቅናቄዎች መሰረት ሆኗል። ለፓን አፍሪካኒዝምና ፓን ብላክ ንቅናቄዎች ሁሉ መሰረቱ የዓድዋ ድል ነበር። በተለያየ የዓለም ክፍል የሚኖሩ ዲያስፖራዎችና የጥቁር ምሁራንም በዓድዋ ድል ምክንያት የተለያዩ ንቅናቄዎችን በመመስረት የአፍሪካን ነፃነት እንዲፋጠን አድርጎታል።

## የዓድዋ ድል ለዛሬው ኢትዮጵያ፣ አፍሪካና ዓለም ሕዝቦች የሚጠቁመው የመልስ አቅጣጫ

የዓድዋ ድል ለዛሬው ኢትዮጵያ ፣አፍሪካና ዓለም ሕዝቦች የሚጠቁመው የመልስ አቅጣጫ እንደሚከተለው ይገለፃል:-

ቀደም ሲል እንደ ተገለፀው የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብር ማኅተም፤ የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተጋድሎ ቀንዲል ነው። የመላው ዓለም ተፈጥሮአዊ ግብር እና ሰብአዊ ክብር የታደሰው፤ በእውነትና በፍትሕ ህልውናና ምልዓት ላይ የተሰካ ትልቅ ጥርስ የተነቀለው በዓድዋ የታላቅ ሕዝቦች ታላቅ ድል ነው። ታላቁ የጥቁር ሕዝቦች ድል (የዓድዋ ድል) በመላው ዓለም ፖለቲካ ላይ ከፍተኛና ዋነኛ ለውጦች አምጥቶአል። ሕ

በዛሬዋ ዘመን ኢትዮጵያ ግን ብዙ ግራ የሚያጋቡ ጥያቄዎች አሉ። የተለያየው ቋንቋቸው፣ ሃይማኖታቸውና ባህላቸው ሳይበግራቸው ዓድዋ ላይ ወራሪን ድል ያደረጉትን ኢትዮጵያውያን ተተኪዎችና የዚህ ዘመን ትውልዶች ግን ከድሉ ያገኙትን ትሩፋትና ገድል እየጠበቁ አይደለም። ትላንታና ድጋፍ ሁኖ ያገለገሉት ቋንቋዎቹ ለዛሬዋ ኢትዮጵያ መሰናክልና ለዝቦቿ ክፍፍል መስኤ እየሆኑ ነው። ትላንት የነበረው ሕብረትና አንድነት መንፈስ በዛሬው ትውልድ ላይ እየታየ አይደለም። ዜጎች በችሎታቸውና በስብዕናቸው ሳይሆን በብሔራቸው እየከበሩና ሰብዓዊነት እየተረሳ የመጣበት ዘመን ላይ እንገኛለን። ተከባብረውና

ተቻችለው ለመኖር የሚያስችሉን እሴቶቻችን እየተሸረሸሩ ይገኛሉ። በጠቅላላው የጥንቱን ድልና ገድል፣ አንድነትና መከባበር በዛሬው ትውልድ ላይ ማየት የሚያስቸግርበት ሁኔታ ላይ ነው ያለነው። ስለዚህም የዓድዋ ድል በዚህ ዘመን ለሚነሱት ጥያቄዎች የሚያስቀምጠው የመልስ አቅጣጫ፣ ልክ እንደ ጥንቶቹ አያት፣ ቅድመ አያቶቻችን ያለምንም የዘር፣ የሃይማኖትና የቋንቋ ልዩነት ለጋራ ዓላማ መቆም እንደምንችል ያስተምረናል። ዜጎቿ መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት ተስኗቸው በድኽነት በሚማቅቁበት በዚህ ዘመን የአንዱን ሌላው እየገፋው ሲያፈናቅለው፣ ሌላኛው ሲሳድደውና ሲያገልለው ይታያል። ከድኽነት ወለል በታች ያለው ሕዝብ የበለጠውኑ ራሱ በሚፈጥራቸው ሰው-ሰራሽ ዕንቅፋቶች ምክንያት አሁንም ድኽነትንና ድንቁርናን፣ ኋላ ቀርነትንና ክፍፍልን፣ ስንፍናንና ልመናን ለልጅ ልጆቹ እያወረሰ ይገኛል። የዓድዋ ድል ሊመጣ የቻለው ግን በተባበረ ክንድ፣ በሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች የተባበረ መንፈስና የጋራ ሞራል፣ በመከባበርና በመቻቻል ላይ በተመሰረተ የጋራ ዓላማ ነበር።

ስለዚህም በዚህ ዘመን ለሚነሱት የኢትዮጵያውያን የመከፋፈልና የጥላቻ መንፈሶች፣ የዘረኝነትና የጎጠኝነት አስተሳሰቦች ትልቅ ትምህርት ነው። ምክንያቱም የቋንቋ ልዩነት ኢትዮጵያውያንን ለጋራ ዓላማ ከመቆም እንደማያደናቅፋቸው ዓድዋ ላይ አይተናል። የቋንቋና ሃይማኖት መብዛት ጌጥና መባረክ እንጂ እርግማን እንዳልሆነ በግልፅ አይተናል። ብዝሃነት ጠላትን ለማሸነፍ የምንጠቀምበት መሣሪያ እንጂ ለክፍፍል የሚሆን ዕቃ እንዳልሆነ በዓድዋ ላይ በተደረገው ዘመቻ ተረድተናል።

በሌላ በኩል  የዓድዋ ድል ለዚህ ዘመን የኢትዮጵያ ጥያቄ እንደመልስ አቅጣጫ ሊቀመጥ የሚችለው ደግሞ ድኽነትን በመዋጋት ረገድ ነው። እንደሚታወቀው አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በድኽነት ዓረንቋ ስር የሚኖር ማህበረሰብ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ግን የተፈጥሮ ሃብት ማጣት አይደለም። ለድኽነታችን ዋናው ምክንያት አስተሳሰባችንና የሥራ ባህላችን፣ ክፍፍላችንና ዘረኝነታችን ምክንያቶቹ ናቸው። ልክ ቅድመ-አያቶቻችን ዓድዋ ላይ እንዳደረጉት ዘመቻ የዚህ ዘመን ትውልድም በድኽነት ላይ ዘመቻ ቢያደርግ ድኽነትን እስካሁን አሽቀንጥረን ጥለነው ነበር። በቅድመ አያቶቻችን ላይ የነበረውን የአንድነት መንፈስ በማጣታችን እስካሁንም ድኽነትን እሽኮኮ ብለን እንገኛለን።

የዓድዋ ድል ለኢትዮጵያውያን የአንድነታችን ምልክት፡ የብሔራዊ ኩራታችን፡ የማንነታችንና የተጋድሎኣችን ማሳያ ምልክት፡ ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ከፍ ብላ

የምትዘከርበትና የምትወደስበት መሣሪያችን ነው። ለኢትዮጵያ ቋንቋዎቿ፣ ባህሎቿ ሃይማኖቶቿና ብዝሃነቷ ጌጦቿ ናቸው። ይህ የኢትዮጵያ ብዝሃነትም የጥንካሬ ምንጭ እንጂ የመከፋፈያ መሳርያ ሁኖ አያውቅም። በልዩነቶቻችን ሊከፋፍለን የመጣው ወራሪ ዓድዋ ላይ የሽንፈትን ፅዋ ተጎንጭቷል።

የዓድዋ ድል ሌላው የዚህ ዘመን ኢትዮጵያ፣ አፍሪካና የዓለም ጥያቄዎች የሚያስቀምጠው የመልስ አቅጣጫ ደግሞ ከስርዓተ ፆታ ጋር የተያያዙ የተለያዩ የተሳሳቱ አመለካከቶችን ለማረም ነው። በዚህ ዘመን በኢትዮጵያ፣ አፍሪካና ዓለም ዙሪያ ከሰርዓተ ፆታ ጋር የተያያዙ የተሳሳቱ አመለካከቶች አሉ። ሴቶች በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይ መሰማራትና ውጤታማ መሆን እንደማይችሉ የሚያስቡ ብዙ የማህበረሰብ ክፍሎች አሉ። ነገር ግን በዓድዋ ድል ሴቶችና እናቶች ቀዳሚ ሚና ነበራቸው። ለድሉ ስኬትም የላቀውን ሚና ወስደዋል። ስለዚህ፣ የዓድዋ ድል ለዛሬው ኢትዮጵያ፣ አፍሪካና ዓለም የሴቶች ጥያቄዎች የሚሰጠው የመልስ አቅጣጫ ላቅ ያለ ነው። የሴቶችን መብት የማያከብሩና ስለ ሴቶች የተሳሳተ አመለካከት ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ሁሉ ከዓድዋ ድል ልምድ መቅሰም ይገባቸዋል። ይህም እንደ አንድ የመልስ አቅጣጫ ይቀመጣል።

የዓድዋ ድል በዚህ ዘመን በዓለም፣ በአፍሪካና በኢትየጵያ ለሚነሱ የመብት ጥያቄዎች ሁሉ የመልስ አቅጣጫን ያስቀምጣል። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያውያን በዓድዋ ላይ ያሸነፉት ሕገ-ወጥነትን፣ አፓርታይድን፣ ግፈኝነትንና ቅኝ ግዛትን ነው። ስለዚህ በዚህ ዘመንም በዓለም ዙሪያ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብታቸው እየተጣሰ ላሉ ግለሰቦች፣ ቡድኖችና ብሔሮች ሁሉ ለመብታቸው እንዲታገሉ የመልስ አቅጣጫ ያስቀምጣል።

ሕገ-ወጥነትን በተባበረ ክንድ ማሸነፍ እንደሚቻል፤ መከባበርን፣ ለአንድነትና ለጋራ ነፃነትና ክብር ራስን መስዋእት ማድረግ እንደሚቻል፤ ዓድዋ የተለያየ ቋንቋ፣ ባህል፣ ሃይማኖትና የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ለጋራ ዓላማና ጥቅም ተከባብሮ መቆም እንደሚችሉ ያሳያል። ልዩነቶቻችን እንዳሉ ሁኖ ለጋራ ዓላማ በክቡር መቆም እንደሚቻል ያሳያል። የሚከፋፍሉትን አደብ ያስገዛል። ሕገ-ወጦችን ማስቆም እንደሚቻል ያሳያል። ለጥያቄዎች መልስ መከባበር፣ መቻቻልና አንድነት መፍትሄ እንደሆነ ይጠቁማል። ኃይል ሳይሆን በአንድነት የተገነባ ሞራል፣ ተስፋና ፍቅር እንደሚያሸንፍ ያረጋግጣል።

ለአፍሪካውያንም እኩልነትንና ደሞክራሲን ያስተምራል። ለነፃነታቸው ትግልም የሞራላቸው ስንቅ ነው። ያልተበረዘው የአፍሪካ ታሪክም ዓድዋ ነው። ሰለዚህም እኩልነትንና መከፋፈልን ማቆምን አንድነትን ያስተምራቸዋል። ለዓለም ሕዝብም እኩልነትንና ነፃነትን ያስተምራቸዋል። አፍሪካውያን ለነፃነታቸው እንዲታገሉ የሞራል ስንቅና የወደፊት ተስፋቸው ሆኗል።

ሲጠቀለል የዓድዋ ድል በዛሬው ኢትዮጵያ፣አፍሪካና ዓለም ለሚነሱ ኢኮኖምያዊ፣ ማሕበራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች በሙሉ መልስ ይሰጣል። ድኽነትን በአንድነትና በጠንካራ መንፈስ በሚደረግ ዘመቻ መርታት እንደሚቻል፤ ከክፍፍልና ጥላቻ ይልቅ አንድነትና መከባበር ለዕድገትና ብልፅግና ጉዞ እንደሚሻል፤ ከዘረኝነትና ጎጠኝነት ይልቅ ሰብዓዊነትና አንድነት እንደሚልቅ፣ ሕገ-ወጥነትና ግፈኝነት ሁሌም ተሸናፊ እንደሆኑና እውነትና ሓቀኝነት እንደሚያሸንፉ፣ በዚህ ዘመንም መብታቸው የሚጣስባቸውና በጫና ስር ላሉ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ በሰላማዊ መንገድ በአንድነት ታግሎ ማሸነፍ እንደሚቻል የመልስ አቅጣጫ ያስቀምጣል።

## ለወ/ሪት ዝምታ ጐርፉ ማስታወሻ

